# ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የተቀናጀ ዘመቻ! (ክፍል አንድ)

ተስፋዬ ለማ  (ክፍል አንድ)

በሕዝቦች ተሳትፎና መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ፍትህ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ የተሰለፈች አገር ለመገንባት ራዕይ ተይዟል፡፡ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ለውጦችን እውን ለማድረግ መልክ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ኢትዮጵያ ለተከታታይ ስምንት ዓመታት ባለሁለት አኃዝ የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገቧን ተከትሎ እድገቱን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ከ2003 - 2007 የሚፈፀም እቅድ ነድፋ በመሥራት ላይ ትገኛለች።

ይህ የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው ቀደም ሲል በአገሪቱ የተመዘገበውን የምጣኔ ሀብት እድገት እንደ መነሻ በመውሰድ፣ ድህነትን ታሪክ በማድረግና ዘላቂ ልማትን የማረጋገጥ ዓላማ አንግቦ ነው።

በዚህ እቅድ የተቀመጠው የልማት አቅጣጫ እንደሚያሳየው ከ2002 - 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሚደረገው ሁለንተናዊ ጥረት የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት እድገት በእጥፍ በማሳደግ ግብርና መር የምጣኔ ሀብት መሠረትን ወደ ኢንዱስትሪ መር ለማሸጋገር የሚያስችል ጽኑ መሠረት መጣል ነው።

እቅዱ ላለፉት ሁለት ዓመታት ሲተገበር ቆይቷል። በ2003 እና በ2004 ዓ.ም የነበረው አፈጻጸም በሚጠበቀው መልክ የተከናወነና ለቀጣይ የሦስት ዓመታት አፈጻጸምም አስተማማኝ መሠረት የጣለ ነው። እቅዱን በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በተጠናከረ መልክ በመፈፀም አገሪቱን በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ማሰለፍ እንደሚቻል መተማመን የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።

በተመሣሣይ ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦችን በተሳካ

መንገድ በማከናወን ግብርና መር ኢኮኖሚውን ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችስተማማኝ መሠረት ይጣላል የሚል እምነት ተይዟል።

የኢንዱስትሪ ልማታችን ኤክስፖርት መር ሆኖ እንዲመራ በእቅዱ ላይ አቅጣጫ ተቀምጧል። የአገሪቱ ምርቶችና የፋብሪካ ውጤቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲወጡ ማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ ተቀምጧል። በሌላ መልኩ ደግሞ የአገር ውስጥ ምርትንና ምርታማነትን በማሳደግ ከተለያዩ የዓለም አገራት ወደ አገራችን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡትን ምርቶች መተካት ነው።

ከዚህ አንጻር በሰፊው ሊሰራባቸው የሚገቡ ዘርፎች ተለይተው የአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አካል ሆነዋል። በስሚንቶ፣ በስኳር፣ በሃይል ምንጭ፣ በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ የመሳሰሉ ዘርፎች የተያዙ እቅዶች ተቀናጅተው ይህንኑ ለማስፈጸም የሚያስችሉ እንደሆነም ይታመናል።

በዚህም መሰረት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል በሚል በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከተያዙት ዓበይት የእንዱስትሪ ግንባታዎች አንዱ የስኳር ልማት ፕሮጄክት ነው።

ኢትዮጵያ ለስኳር ልማት ተስማሚ የአየር ጠባይ ካላቸው የዓለማቸን አገራት በቀዳሚነት ትመደባለች። ለሸንኮራ አገዳ ምርት የሚውል እስካሁን ባለበት ወቅት ሥራ ላይ ያልዋል ሰፋፊ የእርሻ ቦታም ያላት አገር ነች። በዚህ ረገድ አገሪቱ ያላት እምቅ ሃብት በተገቢው መልክ ስራ ላይ በማዋል ድህነትን ለመቅረፍ አጋዥ ሳይሆን ለዘመናት ቆይቷል። በአገሪቱ ቀደም ሲል የነበሩ ጥቂት ፋብሪካዎችን የማስፋፋት ሥራ አልተደረገላቸውም። የሚጠቀሙበት የቴክኖሎጂ ደረጃም የቆየ ከመሆኑ የተነሳ ምርታመነታቸውን ማረጋገጥ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም።

በዚህ ምክንያት የአገሪቱን የስኳር ፍላጎት ማሟላት አልተቻለም። ህዝቡ የሚፈልገውን ያህል አቅርቦት ባለማግኘቱ ይህንን ክፍተት ለመሸፈን መንግስት በከፍተኛ ወጪ ከተለያዩ አገራት ስኳርን ማስገባት የግድ ሆኖበታል። መንግስት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከተለያዩ አገራት እየገዛ በማምጣት እያከፋፈለ ይገኛል። ይህ ችግሩን ለማቃለል ጊዚያዊ መፍትሄ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ቢሆንም ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን ስለማይችል ጉዳዩን በውል የተገነዘበው የኢትዮጵያ መንግስት ዘርፉን ለማልማት ቆርጦ ተነስቷል።

ቀደም ሲል በአገሪቱ የነበሩትን የስኳር ፋብሪካዎች በተገቢው መልክ በማስፋፋትና የያዙትን የምርት

ቴክኖሎጂ በዘመናዊ መሣሪያዎች የመቀየር ተግባር በማከናወን ከእነዚህ ነባር ፋብሪካዎች የሚገኝ ምርትን ማሳደግ የሚቻልበት አቅጣጫ ተይዟል። የነባሮቹን ምርታማነት ከማሳደግ ጎን ለጎን ደግሞ አዳዲስ ፋብሪካዎችን በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመገንባት የሕዝቡን የስኳር ፍላጎት ለማሟላት እየተሰራ ይገኛል።

ከኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን የተገኘ መረጃ እንደሚያሳየው በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ያለው የስኳር ምርት ፍላጎት 5 መቶ ሺሕ ቶን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ እየተመረተ ያለው የስኳር መጠን ግን 3 መቶ ሺህ ቶን ብቻ ነው። በመሆኑ በአቅርቦትና በፍላጎት መካከል ከፍተኛ ክፍተት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል። ይህንን ልዩነት ለማሟላትና ኅብረተሰቡ በስኳር እጥረት ምክንያት የእለት ኑሮው ላይ ጫና እንዳይደርስበት ለማድረግ መንግስሥ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በመግዛት ለሕዝብ እያቀረበ ይገኛል። ይህ መፍትሄ ጊዜያዊ መፍትሄ ነው፡፡ ዘላቂ መፍትሄ ላይም ርብርብ እየተደረገ ነው።

የአገሪቱን የስኳር ፍላጎት በአስተማማኝ መንገድ ለማሟላትና አገሪቱ ለስኳር መግዣ የምታውለውን ምንዛሪ ለማስቀረት የአገር ውስጥ ምርትን ማሳደግ አማራጭ የሌለው መፍትሄ እንደሆነ በመገንዘብ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የስኳር ልማት አንዱ መሠረታዊ የልማት ዘርፍ ሆኖ ተነድፏል።

በዚህ እቅድ መሠረት ነባሮቹን ፋብሪካዎች በተገቢው መንገድ በማስፋፋትና አዳዲሶቹን በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ በማጠናቀቅ የአገሪቱ የስኳር ምርት 2 ነጥብ 25 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ እየተሰራ ነው፡፡ እስካሁን የተከናወነው ተግባር በቀጣይ ሦስት ዓመታት ከሚሰራው ጋር ተጣምሮ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ርብርብ እየተደረገ ይገኛል።

ከዚህ አንጻር አጠቃላይ የስኳር ምርት 2 ነጥብ 25 ሚሊዮን ቶን በማድረስ የአገሪቱ ፍጆታ በመሸፈን ቀሪው ለውጭ ገበያ ማቅረብ ነው። በዚህ መልክ በአገሪቱ መመረት ሲችሉ ከሌሎች አገራት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገዙ ምርቶችን በአገር ውስጥ የመተካት አቅጣጫን ከማሳካት አንጻር አንድ እርምጃ ወደፊት መሄድ ይቻላል። ለስኳር መግዣ የሚውለውን ገንዘብ መቆጠብና ለሌላ ልማት ማዋልም ይቻላል። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ኤክስፖርት መር የሆነውን የኢንዱስትሪ ልማት እድገት ለማገዝ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህ አቅጣጫ ዘርፉ በአገሪቱ የምጣኔ ሀብት ለውጥ ላይ የጎላ ድርሻ እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላል።

የስኳር ልማት ፕሮጀክት የኢንዱስትሪና የግብርና ዘርፎች ከፍተኛ ተመጋጋቢነት እንዲኖራቸው በማገዝ ረገድ ቀላል የማይባል ድርሻ ይኖረዋል።

ከስኳር ምርቱ ጎን ለጎን ለግብርናው ዘርፍ መጠናከር የሚያግዙ ተግባራት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል። በተያያዥነት ሊሰሩ ከሚችሉት ተግባራት አንዱ የኢታኖል ምርት ነው።

ኢታኖልን ከስኳር ፋብሪካዎቹ ተረፈ ምርት በሰፊው በማምረት አገሪቱ ለነዳጅ መግዣ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ ያግዛል። የነዳጅ ሃብትን አፈላልጎ የማውጣት ተግባር በተገቢው መንገድ እያስኬዱ ከስኳር ምርቱ ጎን ለጎን ደግሞ የኢታኖል ምርትን በተገቢው መንገድ በመጠቀም የአገሪቱን ወጪ በተወሰነ ደረጃ መቀነስ ያስችላል።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የኢታኖል ምርቷን በማሳደግና ከቤንዚን ጋር በመቀላቀል ለነዳጅ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ ያስችላታል። ሁለቱን የመቀላለቅልና ሥራ ላይ የማዋል ተግባር በአገሪቱ የተጀመረው በ2001 ዓ.ም ነው፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት ወደ ዚህ ሥራ ከገባችበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን 24 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያህል ወጪ ማዳኗን ከውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያሳያል፡፡

ይህ በአገር ውስጥ የሚመረተው ኢታኖል መጠን ባደገ ቁጥር አገሪቱ ከውጭ የምታስገባውን የነዳጅ መጠን ለመቀነስ ስለሚያስችላት አሁን እየተስፋፋ ያለው የስኳር ልማት ፕሮጀክት ከዚህ አንጻር የሚሰጠው ጠቀሜታም የጎላ ይሆናል።

እስካሁን ድረስ ባለው ተሞክሮ የፊንጫና የመተሃራ ስኳር ፋብሪካዎች ተረፈ ምርትን በመጠቀም 339 ሚሊዮን ሊትር ኤታኖል ማምረት ተችሏል፡፡ ከዚህም 336 ሚሊዮን ሊትር የሚሆነው ከቤንዚን ጋር ተቀላቅሎ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በከፍተኛ ደረጃ ፍላጉት ያለውን ኬሮሲንን በኤታኖል ለመተካት የኤታኖል

ምድጃ ሥራ ሙከራ ተደርጎ በአነስተኛና ጥቃቅን ተሰርቶ እንዲሰራጭ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ከኢታኖል ምርት ጎን ለጎን የስኳር ፋብሪካዎቹ በመቋቋማቸው ምክንያት የሚገኘው ሌላው ጥቅም የዓሣ ምርት ነው። በእነዚህ ትላልቅ የስኳር ፋብሪካዎች በሚገነቡ ሰው ሰራሽ ሐይቆች ዓሣን በሰፊው ማራባት ይቻላል። በዚህ መልክ የአካባቢው ኅብረተሰብ በሁለት መልክ ተጠቃሚ ይሆናል። አንደኛ ዓሣን እያራባ ለምግብነት መጠቀም ሌላው ደግሞ ዓሣን በሰፊው እያመረተ ለገበያ ማቅረብ ነው።

የተፈጥሮ ሐይቆች ባሉባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የዓሣ ምርትን ከራሳቸው ምግብ አልፎ ለገቢ ማስገኛም የሚጠቀሙበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይህንን ተሞክሮ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች በሚሰሩባቸው አካባቢዎች በማስረጽ ሰው ሰራሽ ሐይቆቹን የዓሣ ምርትን ለማስፋፋት በመጠቀም ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ እንስሳትን የማድለብ ተግባር ይሆናል። በእነዚህ የስኳር ፋብሪካዎች አካባቢ የሚኖሩ አርሶና አርብቶ አደሮች የፋብሪካዎቹን ተረፈ ምርቶች እየተጠቀሙ እንስሳትን እንዲያረቡና እንዲያደልቡ ይደረጋል። አርብቶ አደሩ ከዚህ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ የሚሆንበት ክፍተት አለመኖሩን መገንዘብ ይቻላል።

አካባቢው ወደ ከተማነት ስለሚቀየርና እንደ መንገድ የመሣሠሉ መሠረተ ልማቶች ስለሚስፋፉ የሚያደልቧቸው እንስሳት ለገበያ የማቅረብ ችግር አያጋጥማቸው። ይህ ቀደም ሲል በመሠረተ ልማት ምክንያት ምርታቸውን ለገበያ አቅርበው በተመጣጣኝ ዋጋ ለመሸጥ ያጋጥማቸው የነበረውን ችግርም ጎን ለጎን የሚፈታ ይሆናል።

አርሶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩ በእነዚህ የስኳር ፋብሪካዎች መከፈት ምክንያት የሚያገኘው ሌላው ጥቅም ደግሞ መስኖ ገብ እርሻ ልማትን ማከናወን ነው። መስኖ ገብ ማሣዎችን በማስፋፋት በዓመት ሦስት ጊዜ እንዲያመርቱ ይደረጋል።

በዚህ መልክ አርሶ አደሩ የግብርና ምርቱን ለማሳደግ የሚያስችል ሁለንተናዊ ድጋፍ ይደረጋል።

የስኳር ልማት ፕሮጀክቶቹ የአገሪቱን የስኳር ፍላጎት በማሟላት የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት በተጨማሪ በሚቋቋሙበት አካባቢ የሚኖረውን ኅብረተሰብ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል። በዚህ የተቀናጀ እንቅስቃሴ ኅብረተሰቡ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ይሆናል።

ባለፉት ሁለት የእድገትና የትራንስፎርማሽን ዓመታት በነባሮቹ ላይ የሚደረገው የማስፋፋት ፕሮግራምም ሆነ አዳዲሶቹን የመገንባት ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እየተከናወነ ይገኛል።

ፋብሪካዎቹ በሚቋቋሙባቸው አካባቢዎች የተለያዩ መሠረተ ልማቶች እየተሟሉ ይገኛሉ። ለኅብረተሰቡ በቂ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የመንገድ፣ የጤና፣ ትምህርት ቤቶች፣ መንደሮችና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶች እየተሟሉ ነው። ከፋብሪካዎቹ በቀጥታ የተያያዙ እንደ ግድብና ውኃን ለመጥለፍ የሚያስችሉ ሥራዎችም ሳይቆራረጡ በመከናወን ላይ ናቸው።

እያንዳንዱ የስኳር ልማት ፕሮጀክት ለሕዝቡ የሚሰጠው ጥቅምና ያለበት ደረጃ በቀጣይ የሚቀርብ ቢሆንም እነዚህን ለአገሪቱ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ለማደናቀፍ በተለያዩ የአገሪቱ ጠላቶች በየጊዜው እየተነሱ የሚያራግቡት እርባና የለሽ ዘገባዎችን በግርድፉ አይቶ ማለፍ ተገቢ ይሆናል።

በተለይ ከወልቃይትና ከኦሞ ኩራዝ ፕሮጀክቶች ጋር ተያይዘው በተደጋጋሚ እየተነሱ ያሉት መሠረት የለሽ ውንጀላዎች የዋልድባ ገዳም ተደፈረ፤ ፈረሰ የሚል እና በኦሞ ኩራዝ የሚኖሩ የቦዲና ሙርሲ ብሔረሰቦች ማንነታቸውን ያጣሉ የሚሉ ይገኙባቸዋል።

በዋልድባ ገዳም እየተነሳ ያለውን ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ የአገሪቱን ልማት ለማደናቀፍ ኃይማኖትን በሽፋንነት የመጠቀሙ ቅጥያ መሆኑ እሙን ነው። እየለማ ያለው የስኳር ልማት ለአካባቢው ሕዝብም ሆነ ለዋልድባ ገዳም የሚኖረው ጠቀሜታ ቀላል አይደለም። የገዳሙ ማኅበረሰብ በአካባቢው ከሚገነቡ መሠረተ ልማቶችና ከሚገኘው ልማት ተጠቃሚ ከመሆኑም ባሻገር የገዳሙ ኅቢኚዎች እስካሁን ከነበረው በተሻለ መልኩ ስለሚያድግ የገዳሙ ገቢም በዚያው ልክ የሚያድግ ይሆናል፡፡

ከአካባቢው የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ገዳሙ በግንባታው ምክንያት እንደማይነካ ነው። ምናልባትም በግንባታው ምክንያት የሚነካው በገዳሙ የሚኖሩ አባቶች ለእርሻ ይጠቀሙበት የነበረው መሬት የተወሰነው ክፍል ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ተለዋጭ መስኖ ገብ የሆነ መሬት በልዋጭ ለሞነከሣቱ ይሰጣል። እስካሁን ያገኙት ከነበረ የእርሻ ምርት በተሻለ መልክም በዓመት ሦስት ጊዜ ማምረት የሚችሉበት ሁኔታ ስለሚፈጠር የበለጠ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ ሊያደርጋቸው አይችልም።

የኦሞ ኩራዝ ማኅበረሰቦች ደግሞ ቋሚ የሆነ መኖሪያ መንደር አልነበራቸውም። እስካሁን የሚኖሩት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ነው። ውኃና የግጦሽ መሬት ፍለጋ እንስሶቻቸውን ይዘው እየተዘዋወሩ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመሆናቸው ተፈናቀሉ የሚያሰኝ እውነታ የለም። ይሁንና የማስፈሩ ሥራ የሚከናወነው አንድም አካባቢውን ለማልማት ሁለትም የአካባቢውን ማኅበረሰቦች በመንደር አሰባስቦ የሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶችና ለኑሯቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር በማሟላት ከነበራቸው ኑሮ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩበት ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

በወልቃይት ከመንደር ለሚነሱ ጥቂት ዜጎች አስፈላጊውን ካሣ በመክፈልና ተለዋጭ ሥፍራ በመስጠት እየተከናወነ ነው። በዚህ ዙሪያ ከሕዝቡ ጋር በቂ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ሕዝቡ የልማቱን ጠቀሜታ ተገንዝቦ ከመንግሥት ጎን ተሰልፎ እየሰራ ይገኛል። እውነታን ይህንን ሲመስል በተለያዩ አካባቢዎች እየተገነባ ያለው የስኳር ልማት ከሕዝብ ፍላጎት ውጭ እየተከናወነ እንዳለ አስመስሎ ማራገቡ ለሌላ ድብቅ አጀንዳ ካልሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታስቦ እንዳልሆነ እሙን ነው። ይህ ደግሞ ያልበላህን የማከክ ያህል ነው።

በእነዚህ አካላት እየተሰራጩ ያሉት የሀሰት ዘገባዎች የስኳር ልማት ፕሮጀክቶቹ ለኅብረተሰቡ ሊያስገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታ በመድፈቅ ችግር መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ኅብረተሰቡ ልማቱን ይቃወም ይሆናል የሚል ግምት ተይዞ በአጠቃላይ የአገሪቱን ልማትና ግስጋሴ በተለይ ደግሞ የስኳር ልማት አቅጣጫችንን ለማሳት የተቀናጀ እኩይ ተግባር ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቅመውንና የማይጠቅመውን ለይቷል። በአልቧልታና መሠረት በሌለው ዘገባ ምክንያት የሚደናገርበት ዘመንም አክትሟል። የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አገሪቱ ከድህነት ለማላቀቅና ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚያሸጋግር መሠረት የሚጣልበት እቅድ መሆኑን በተገቢው መንገድ በመገንዘብ እጅና ጓንት ሆኖ ለስኬቱ እየተረባረበ ይገኛል።

የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች ባሉባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎች የስኳር ልማቱ ለአገሪቱ ከሚሰጠው ጥቅም ተጠቃሚ ከመሆን ባሻገር በስኳር ልማቱ መልማት ምክንያት ጎን ለጎን ተጠቃሚነታቸው የሚረጋገጥ በመሆኑ ልማቱን የማፋጠን አቅጣጫ እየተከተሉ ይገኛሉ። በመሆኑም

ልማቱ በተፋጠነ መንገድ እንዲከናወን የድርሻቸውን እየተወጡ ነው።

ስለሆነም ለእንዲህ ዓይነት መሠረት የለሽ ዘገባ የሚሰጡት ጆሮ አይኖራቸውም። ይልቁንስ መንግሥት ድህነት ላይ እያደረገ ያለውን የተቀናጀ ዘመቻ ለማጠናከር ድጋፉን ይለግሳል እንጂ።

የስኳር ልማት በኢትዮጵያ ጠላቶች እኩይ ተግባር ሊቀለበስ አይችልም። ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የተጀመረው የተቀናጀ ዘመቻ በሕዝቡ አንድነትና ተሳትፎ እውን ይሆናል። የእያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት አጠቃላይ ገጽታና በአሁኑ ወቅት ያለበትን ደረጃ በቀጣይ ክፍሎች ለማየት እሞክራለሁ።